**ረቂቅ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር _____/ 2016**

**የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2013 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀፅ 72 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር ---/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

1) የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

(ሀ) "ኮሚሽን" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 (እንደተሻሻለ) የተቋቋመው የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፤

(ለ) "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፤

(መ) "አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ነው፤

(ሠ) "የታክስ አስተዳደር አዋጅ" ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2016" ነው፤

(ረ) " የታክስ ባለስልጣን" ማለት እንደሁኔታው የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት የውክልና ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ነው፤

(ሰ) " የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ምዕራፍ ሁለት መሰረት የሚሰጥ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ነው፤

(ሸ) “የተጨማሪ እሴት ታክስ” ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር1341/2016 የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

2) በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላት እና ሃረጎች የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር እንደአግባብነቱ በአዋጁ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን

1) በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ውክልና ሊሰጥ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፤

(ሀ) የገቢዎች ሚኒስቴር በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር ውስጥ ቢሮ የሌለው ከሆነ፤

(ለ) በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር የኢንተርኔት ግንኙነት ውስን በመሆኑ ወይም ጭራሹንም የሌለ በመሆኑ ምክንያት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ታክስ ለማስታወቅ እና ለመክፈል የማይችሉ ሆኖ ከተገኘ፤

2) በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት የሚሰጠው ውክልና የሚያገለግለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብ ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስን መወሰን፤ የግብአት ታክስን ክሬዲት ማድረግ፤ ተመላሽ መስጠት፤ የታክስ ሕጉን መሠረት በማድረግ አቅርቦቶች ከታክሱ ነጻ እንዲሆኑ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን መወሰንን ጨምሮ ሌሎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ሃላፊነቶች በሙሉ የገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናሉ፡፡

3) ታክሱን ለመሰብሰብ ውክልና የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ በውክልናው መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሰበሰበውን ታክስ ወሩ በተጠናቀቀ በአምስት ቀን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

4) የገቢዎች ሚኒስቴር ከግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ የየክልሉ ድርሻ የሆነውን ወሩ በተጠናቀቀ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የገቢው ባለቤት ለሆነው ክልል ማስተላለፍ አለበት፡፡

5) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልል ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ረገድ ሊያከናውኑት የሚገባ ተግባር በፌዴራል እና በክልል የገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች በሚፈረም የጋራ መግባቢያ ስምምነት ይወሰናል፡ ፡

## ክፍል ሁለት
## ምዝገባ

### 4. የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት

ለተመዘበ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 14(5) መሰረት የሚሰጠው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን የሚጨምር መረጃ ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ) የተመዘገበውን ሰው ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
ለ) ለተመዘገበው ሰው የሚሰጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር፤
ሐ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበትን ቀን፤ እና
መ) ምዝገባው የጸና የሚሆንበትን ቀን።

### 5. ምዝገባን ስለማገድ

1) ለአዋጁ አንቀጽ 16(8) አፈጻጸም የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባው የታገደበት ሰው፤ ምዝገባው በታገደበት ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን መፈጸም የለበትም:-
   ሀ) ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት መፈጸም፤
   ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፤ የክሬዲት እና የዴቢት ሰነድ መቁረጥ፤
   ሐ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲሰጠው ወይም የግብአት ተመላሽ እንዲፈቀድለት መጠየቅ፤ ወይም
   መ) ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በሚያከናውንበት በማናቸውም ሰነድ ወይም ድረ-ገጽ፤ የማሕበራዊ ሚዲያ አድራሻ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግብይት በሚያከናውንበት መድረክ የተመዘገበ ሰው መሆኑን መግለጽ፤

2) ምዝገባው የታገደበት ሰው የምዝገባው መታገድ በጸናበት ቀን በአዋጁ አንቀጽ 48 መሰረት ወደፊት የተሸጋገረ ክሬዲት ሊደረግ የሚችል ሂሳብ ያለው እንደሆነ ክሬዲት ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ እገዳው እስከሚሻር ድረስ እንዲቆይ ሆኖ እገዳው ሲነሳ ተፈጻሚ ይሆናል።
3) ምዝገባው የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማከናወኑን የማይቀጥል ከሆነ ምዝገባው ታግዶ ባለበት በማናቸውም ጊዜ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።
4) የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች አቅርቦት ለመቀጠል ከፈለገ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

15) የተመዘገበ ሰው ዋና መስሪያ ቤት ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፤ የስራ ክፍል፤ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ምዝገባ እንዲሰረዝ ለታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ ሊያመለክት ይችላል።ምዝገባው የሚሰረዘው የሚከተሉት ሲሟሉ ይሆናል፦

ሀ) የታክሱ ባልስልጣን ከዚህ ያነሰ ጊዜ ካልፈቀደ በስተቀር፤የቅርንጫፍ የተለየ ምዝገባ ቢያንስ ለሁለት አመት ጸንቶ መቆየት አለበት፡

ለ) ማናቸውም ኩባንያ ወይም ቅርንጫፍ ለቅርንጫፍ ምዝገባ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላቱን ያቋረጠ እንደሆነ ኩባያው ከቅድመ-ሁኔታዎች አንዱ መሟላቱ በተቋረጠ በ 30 ቀናት ውስጥ ይህንን ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

ሐ) የታክሱ ባለስልጣን ለቅርንጫፍ ምዝገባ የተቀመጡት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው የተቋረጠ ወይም ለመንግስት ገቢ ደህንነት አስፈላጊ መስሎ ከታየው የቅርንጫፍ ምዝገባን ለመሰረዝ ይችላል።

መ) የታክሱ ባለስልጣን የቅርንጫፍ ምዝገባ የሚቀጥል መሆን ያለመሆኑን የመወሰን ሙሉ ስልጣን አለው።

ሠ) የቅርንጫፍ ምዝገባ መሰረዝ የጸና የሚሆነው የታክሱ ባለስልጣን ምዝገባው መሰረዙን ለማስታወቅ በሚሰጠው ማስታወቂያ ከተገለጸው ቀን አንስቶ ይሆናል።

## ክፍል ሶስት
## አቅርቦቶች

### 8. የአደራ ሽያጭ እና በውክልና ስልጣን ደረጃ ስለማስተላለፍ

1) የእቃው ባለቤት (ሻጭ) እቃውን በአቅርቦት ወይም በተመላሽ (የአደራ ሽያጭ) ለሌላ ሰው መስጠቱ ግብይት እንደተፈጸመ አያስቆጥርም።
2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተመለከተው የእቃ አቅርቦት ግብይት ተፈጽማል የሚባለው ባለቤቱ የእቃውን ባለቤትነት ወደ ገዢው ሲያስተላልፍ ይሆናል።
3) በውክልና ስልጣን ደረጃ እቃ ለአንድ ሰው ሲተላለፍ ግብይት እንደተፈጸመ አይቆጠርም።
4) ሚኒስቴሩ ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም የሚያግዝ መመሪያ ያወጣል።

### 9. ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን እቃ ወጪ ስለማድረግ

1) በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 (እንደተሻሻለ) በተደነገገው መሰረት እቃ ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን ወጪ ሲደረግ ወይም የእቃ አቅርቦት ሲፈጸም በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የእነዚህ እቃዎች አቅርቦት እንደተፈጸመ ይቆጠራል።

1) የተመዘገበ ተጠቃሚ በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው የኤሌክትሪክ አቅርቦት በሌለ ጊዜም ያለማቋረጥ መጠቀም እንዲችል ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ አለበት፡፡

2) የተመዘገበው ተጠቃሚ በማናቸውም ምክንያት በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው መጠቀም ያልቻለ እንደሆነ፦

ሀ) በመሳሪያው መጠቀም እንዳይችል ያደረገው ሁኔታ በተፈጠረ በ24 ሰአት ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባላስልጣን ማስታወቅ አለበት፤

ለ) በመሳሪያው መጠቀም ባልቻለበት ጊዜ ውስጥ ያከናወነውን አቅርቦት በማናቸውም ሌላ ዘዴ መመዝገብ፤ እና

ሐ) በመሳሪያው መጠቀም ባልቻለበት ጊዜ ውስጥ ላከናወነው ግብይት ለአቅርቦቱ ተቀባይ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚመርጠው የማተሚያ ድርጅት የታተመ በእጅ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ መስጠት፤ አለበት፡፡

3) የተመዘገበው ተጠቃሚ በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው መጠቀሙን ሲቀጥል፤በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) (ለ) መሰረት ያከናወነውን አቅርቦት በዝርዝር በመሳሪያው ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

## 27. የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ዝግጁነት

1) የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ የተመዘገበ ተጠቃሚ፦

ሀ) የሽያጭ ተግባር በሚያከናውንባቸው ቦታዎች ሁሉ የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ እንዲኖር ማድረግ፤

ለ) የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያዎችን ለመቆጣጠር የተመደቡ ሰራተኞች ስራቸውን እንዲያከናውኑ ማገዝ፤

ሐ) መሳሪያው ሁል ጊዜም ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ወቅታዊ የሆነ እድሳት እንዲደረግለት ማድረግ፤

መ) የተመዘገበው ተጠቃሚ ለሚጠቀምበት የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ(ዎች) የተደረገውን እድሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ፤ የሚያሳይ መዝገብ ማቋቋም እና ጠብቆ ማቆየት፦

(i) የመሳሪያውን እድሳት ስራ ያከናወነውን ሰው ስም እና አድራሻ፤ እና

(ii) የመሳሪያውን እድሳት ስራ ባከናወነው ሰው ፊርማ የተረጋገጠ በእያንዳንዱ እድሳት በተደርገበት ጊዜ የተከናወነውን እድሳት የሚያሳይ ዝርዝር፤

ሠ) የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት።

2) የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያውን እድሳት የሚያከናውነው ሰው የመስሪያውን አሰራር ለመለወጥ የተከናወነ ተግባር መኖሩን ሲደርስበት ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

## 28. በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀምን ስለማቋረጥ

1) የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በኤሌክትሮኒክ ፍስካል መሳሪያ መጠቀምን ማቋረጥ ከፈለገ ይህንኑ ለታክሱ ባላስልጣን ማስታወቅ አለበት፦

   ሀ) የተጠቃሚው የንግድ ስራ ከተዘጋ፤
   ለ) ታክስ የሚከፈልባቸውን አቅርቦቶች ማከናወን ካቆመ፤
   ሐ) ሌሎች ምክንያቶች ካሉ፤

2) በዚህ አንቀጽ ሙስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርበው ማስታወቂያ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ከኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ መጠቀም ከመቋረጡ ከ30 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን መቅረብ አለበት።

3) የተመዘገበው ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ለታክሱ ባለስጣን ማስታወቂያ ካቀረበ ፤ የታክሱ ባለስልጣን ማስታወቂያ በቀረበ በ21 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያውን አገልግሎት ማቋረጥ አለበት። የታክሱ ባለስልጣን በ21 ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ በመሳሪያው መጠቀም እንደተቋረጠ ይቆጠራል።

## 29. በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የሚዘጋጅ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ

በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ የሚዘጋጅ የኤሊክትሮኒክ የታክስ ደረሰኝ፤ የግሬዲት ኖት እና የዴቢት ኖት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

ሀ) እንደሁኔታው በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 እና 18 የተዘረዘሩትን መረጃዎች፤

ለ) የመሳሪያውን የተለየ መለያ፤

ሐ) እንደአግባብነቱ የታክስ ደረሰኙን፤ የክሬዲት ኖቱን ወይም የዴቢት ኖቱን የተለየ መለያ፤

መ) የፈጣን ምላሽ ( ፈም) ኮድ፤ እና

ሠ) የገቢዎች ሚኒስቴር  በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝራቸው ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፤

## 30. የመረጃ ደህንነት እና መረጃን ስለማስተላለፍ

የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የሚከተሉትን ማከናወን የሚችል መሆን አለበት፦

ሀ) የታክስ ደረሰኝ፤የክሬዲት እና የዴቢት ኖት መረጃዎችን እንዲሁም የየእለቱን መጨረሻ የማጠቃለያ መረጃ የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሰረት ወደታክስ ባለስልጣኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአት ማስተላለፍ፤

ለ) በውስጡ የተከማቸውን መረጃ ማተም እና መስጠት፤

ሐ) በውስጡ የያዘውን መረጃ ለማየት ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ሊረዱት በማይችል አኳኋን መረጃን በውስጡ ማከማቸት፤

መ) በውስጡ ያለው መረጃ አስተማማኝ መሆን፤

ሠ) የተፈቀደላቸውን ሰዎች ማንነት ማረጋገጥ የሚችል፤

ረ) በመሳሪያው የተከናወኑ ተግባራትን በሙሉ መዝግቦ የሚያዝ፤

ሰ) ለኣያንዳንዱ የታክስ ደረሰኝ የተለየ መለያ መስጠት የሚችል፤

## 31.  ይህንን የደንቡን ክፍል በመተላለፍ የሚጣል ቅጣት

1) የዚህን የደንቡን ክፍል ድንጋጌዎች ተላለፎ የተገኘ ማናቸውም ሰው በተላለፈው በእያንዳንዱ ድንጋጌ ልክ ብር 100,000 ( አንድ መቶ ሺህ ብር) አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡፡

2) የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ በትክክል እንዳይሰራ ለማድረግ የነካካ፤ ያመቻቸ፤ ወይም በአሰራሩ ጣልቃ የገባ ማናቸውም ሰው በወንጀል ተጠያቂ ከመሆኑ በተጨማሪ ብር 200,000 ( ሁለት መቶ ሺህ ብር ) አስተዳደራዊ መቀጫ ይቀጣል፡፡

## 32. በኤሌክትሮኒክስ የፊስካል መሳሪያ ለመጠቀም የመጋገሪያ ድንጋጌዎች

1) ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰነው ቀን አንስቶ በ12 ወራት ውስጥ በዚህ የደንቡ ክፍል በተወሰነው መሰረት መፈጸም አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት መፈጸም ያልቻለ ሰው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ለማቅረብ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ ቢያንስ በንኡስ አንቀጽ(1)የተመለከተው የ12 ወራት የጊዜ ገደብ ለመጠናቀቅ 30 ቀናት ሲቀረው ለታክሱ ባለስልጣን መቅረብ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚፈቀደው የጊዜ ገደብ ማረዘሚያ ፈቃድ ከስድስት ወራት ሊበልጥ አይችልም፡፡

# ክፍል ስምንት
# አስተዳደራዊ እና የስነ ስርአት ድንጋጌዎች

## 33. በአበዳሪዎች የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ

1) ይህ የደንቡ ክፍል ለአዋጁ አንቀጽ 42(5) ትክክለኛ አፈጻጸም የሚያገለግል ነው፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## ዜሮ የማስከያ ልክ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው አቅርቦቶች

### 47. ወደውጭ ስለሚላኩ እቃዎች

በአዋጁ አባሪ 1 ክፍል 1 እና 2 መሰረት ወደውጭ የሚላኩ እቃዎች እና ተዛማጅ አገለግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆንላቸው ማድረግ የሚቻለው የታክሱ ባለስልጣን በሚያዘው መሰረት ላኪው በወጪ እቃዎች ወደብ እቃዎቹን እና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ለይቶ ሲያቀርብ ይሆናል።

### 48. ለላኪ እቃዎችን ስለማቅረብ

1) በአዋጁ አባሪ 1 ክፍል 4 ተራ ፊደል (መ) "*ዕቃዎችን ወደውጪ መላክ*" ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም የተመዘገበ ሰው ለውጭ ገበያ ለሚያቀርብ ለሌላ የተመዘገበ ሰው (ላኪ) የሚያቀርባቸው እቃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ለውጭ ገበያ የተላኩ እንደሆነ ይቆጠራል፦

   ሀ) የእቃውን አይነት እና አግባብነት እስካለው ድረስ የላኪውን መደበኛ አሰራር እንዲሁም ምክንያታዊ የሆነውን የጉዳዩን አፈጻጸም ከግምት ውስጥ በማስገባት ላኪው እነዚህን እቃዎች እንደተረከበ ወዲያውኑ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ከሆነ፤

   ለ) ላኪው እነዚህን እቃዎች የተረከበው ለፍጆታ፤ ለመጠቀሚያ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ ለማቅረብ ካልሆነ፤

   ሐ) የእቃዎቹ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ እቃዎቹን ለማጓጓዝ አስፈላጊ ካልሆነ ወይም የማጓጓዙ አካል ካልሆነ በስተቀር እቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደገና ለመሰራት፤ ለመለወጥ ወይም ተሻሽለው ለመሰራት የማይውሉ ከሆነ፤እና

   መ) ላኪው እቃዎቹ ለውጭ ገበያ የተላኩ መሆኑን የሚያስረዱ የታክስ ባለስልጣኑን የሚያሳምኑ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት፤

2) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም፦

## 57. የእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት

1) ይህ የደንቡ ክፍል በአዋጁ አባሪ 2 አንቀጽ 2 ተራ ቁጥር (1) "ለፋይናንስ አገልግሎት" ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም የሚያገለግል ነው፡፡

2) የታክሱ ባለስልጣን ለእስልምና የፋይናንስ ስርአት የተደነገጉትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚከተሉት ተግባራዊ ያደርጋል፦

   ሀ) የፋይናንሱ ስራ የሚያካትታቸውን የተለያዩ አቅርቦቶች ለይቶ ማወቅ፤

   ለ) በእስልምና የፋይናንስ ስራ ውስጥ የማይካተቱ አቅርቦቶችን የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መወሰን፤እና

   ሐ) በእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት የሚቀርቡ አገልግሎቶች አንድ አይነት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

3) ለእስልምና የባንክ አገልግሎት አቅርቦቶች የሚኖረው የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻደም እስልምና ነክ ካልሆኑ የባንክ አገልግሎት አቅርቦቶች ጋር እኩል ካልሆነ፤ የተጨማሪ እሴት ታክሱ አፈጻጸም የአቅርቦቱን አላማ፤ ባህሪያት እና ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል፡፡

4) ሚኒስቴሩ የአንድን የእስልምና የባንክ አገልግሎት አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ " የእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት" ማለት የሸሪያ ህግ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ የፋይናንስ አቅርቦት አገልግሎት ውል ነው፡፡

## 58. የሐይማኖት ነክ አገልግሎት

1) ለአዋጁ አባሪ 2 አንቀጽ 1(ቀ) አፈጻጸም በሃይማኖት ተቋም የሚሰጡ የሃይማኖቱ ስርአት አንድ ክፍል የሆኑ አቅርቦቶች የሃይማኖት ነክ አገልግሎት ይባላሉ፡፡

2) የሃይማኖት ተቋም የሚያቀርባቸው እና ከግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ የሆኑ አቅርቦቶች ወይም የሃይማኖቱ ስርአት አካል ያልሆኑ አቅርቦቶች የሃይማኖት ወይም ቤተክርስቲያን ነክ አገልግሎት አይባሉም፡፡ የሃይማኖቱ ተቋም የሚያቀርባቸው የዚህ አይነት አቅርቦቶች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 12 ለምዝገባ ከተቀመጠው የገንዘብ በላይ ከሆነ የሃይማኖት ተቋሙ ለምዝገባ ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 62. የአካል ጉዳተኞችን የሚቀጥሩ ሰዎች

1) የአዋጁ አባሪ 2 አንቀጽ (1) (1) (ኘ) የአካልጉዳኞችን ወይም የአእምሮ ጉዳተኞችን ቀጥረው በሚያሰሩበት ድርጅት የእቃ እና የአገልግሎት አቅርቦት በማከናወን ላይ ለሚገኙ ሰዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2) በአዋጁ አባሪ 2 አንቀጽ (1) (1) (ኘ) የተደነገገው የ60% ተፈላጊ መስፈርት ከአጠቃላይ የድርጅቱ ሰራተኞች መካከል የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኞችን ብዛት በመቶኛ በመውሰድ የሚሰላ ሲሆን፤ ይህ ቁጥር ሁልጊዜም የተሟላ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ንኡስ አንቀጽ አላማ "ሰራተኛ" ቋሚ፤ የከፊል ጊዜ እና ጊዜያዊ ሰራተኛን ይጨምራል፡፡

## 58. ሰብአዊ እርዳታ

የአዋጁ አባሪ 2 አንቀጽ 1 (ተ) እና የአባሪ 3 ተራ ፊደል (ኘ) የአደጋ መካከል የብሄራዊ የስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የተፈጥሮ አደጋ፤ የኢንዱስትሪ አደጋ ወይም ሌላ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ባደረገው ጥሪ መስረት ወደአገር ለሚገቡ እና አገር ውስጥ ለሚቀርቡ እቃዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አስራ ሶስት
## ከታክሱ ነጻ የሆኑ ወደአገር የሚገቡ እቃዎች

## 59. ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እንዲውል ወደአገር የሚገባ ወርቅ

የወርቁ የጥራት ደረጃ ወይም የሚቀርበበት ቅርጽ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ወደአገር ገብቶ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ በአዋጁ አባሪ 3 አንቀጽ 1(ረ) መሰረት ከታክሱ ነጻ ይሆናል፡፡

## ክፍል አስራ አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 60. የተሻሩ ህጎች

1) የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1994 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

2) የተሻረው ደንብ ይህ ደንብ የጸና ከመሆኑ በፊት ባሉ የሂሳብ ጊዜዎች ለተከናወኑ ግብይቶች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

